GreenFire
Igniting your Potential

This Newsletter is produced and distributed Free of charge by **Motion Consultancy and Training PLC.**

ISSUE 2020 VOL 03
MARCH 2020

Monthly Newsletter powered by **Motion Consultancy & Training PLC.**

እንዳይታለሉ!



በሩሲል ጌታቸው

መቼም መታለል ወይንም መሸወድ የሚፈልግ ሰው ያለ አይመስለኝም። ታዲያ አለመፈለጉ ብቻ በቂ አይደለም በተለይ ደግሞ የዘመኑ ስልጣኔ በሚያመጣቸው ነገሮች ምን ያህል እንታለል ይሆን? በዚህ ጽሁፌ ወዴት እያመራሁ እንደሆነ ይገምታሉ ብዬ አስባለሁ። ዓለም በሙሉ በየእለቱ ስለሚጠቀምበት ኢንተርኔት ላይ ስላሉ የተለያዩ የማጭበርበሪያ ነገሮችና እንዴት እራሳችንን መጠበቅ እንደምንችል ለማሳወቅ ያህል ይቺን አጭር ጽሁፍ ይዤላችሁ ቀርቤያለሁ።

በመጀመሪያ ግን ኢንተርኔት ማለት ምንድን ነው ከሚለውና ባለቤቱስ ማን ነው የሚለውን ብናወራ ለጠቅላላ እውቀታችን ይጠቅመናል። ኢንተርኔት ማለት በአጭሩ በአለም ዙሪያ በተለያዩ አገራት ያሉ በጣም ብዛት ያላቸው ኮምፒውተሮች ግንኙነት በመፍጠር መረጃዎችን መቀባበል መቻላቸው ነው። ታዲያ

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

In this Issue

Pg 1 እንዳይታለሉ!
Pg 3 ከማማረር ማሳመር
Pg 6 WHY Motion?
Pg 7 ሰውን እንዳይችል የሚያደርገው ምንድን ነው?
Pg 8 Intersting Facts
Pg 9 A place to be

GreenFire

Dear, Valued Readers

First and for most I would like to thank you for taking time from your precious day to read our monthly newsletter titled Green Fire. On behalf of the Green Fire newsletter editorial team, and the parent company Motion Consulting & Training Staff it's my pleasure to provide you this newsletter free of charge.

Our great editorial team has worked hard in producing this newsletter with all the information that we believe will be a value to your life. Green Fire is produced and edited at Motion Consulting and Training headquarters and distributed via email and through our Telegram channel as well as Facebook page monthly.

If you have any comments, questions, or you would like to contribute to our newsletter, just send us an email.
greenfireNL@gmail.com

Thank you

Fasil Getachew
Chief Editor of Green Fire Newsletter



Editorial Team

Chief Editor: Fasil Getachew

Content Producer: Abebe Legesse, Berhanu Rabo, Yonatan Gena, Fasil Getachew, Temesgen Abiy

Layout Designer: Fasil Getachew

Proof Reader: Abebe Legesse, Berhanu Rabo, Rahel Teshale, Temesgen Abiy

Copy Writer: Fasil Getachew

Production: Motion Consultancy & Training PLC.

ከማማረር ማሳመር

በብርሃኑ ራቦ

ሕይወት የግል መንገድ ናት። እኛ ቆመን ሌላው ሊሄድልን አይችልም። ሌላው ሄዶ እኛ ልንደርስ አንችልም። ቢመርም ቢጣፍጥም የራሳችንን ዕጣ ፈንታ የምናበስለው እኛው ነን። ሰው ከቤተሰብ ሃብትን እንጂ ደስታን ሊወርስ አይችልም። ገንዘብ እንጂ ግንዛቤ አይወረስም። እናም ፈጣሪ የሰጠንን ዘመን አብረን ዘምነን በየቀኑ መስራት ያለብንን ሰርተን መኖር ያለብንን ኖራን ለማለፍ ምስጢሩ ማማረር ሳይሆን ማሳመር ነው። ይህ ማለት ማንኛውም ሰው ምክንያት ከመደርደር ታቅቦ ቢያንስ ስለ ገዛ ሕይወቱ መቶ ፐርሰንት ሃላፊነት መውሰድ እንደሚገባው መረዳት ይጠበቅበታል።

በዚህች ምድር ላይ ትልቁ መኖር በጥበብ መኖር በእውቀት መቅደም ነው። በጥበብ የሚኖረውን በእውቀት የቀደመንን በምንም መቅደም አይቻለንም። ከባዶ ጫንቅላት ባዶ ኪስ በእጅጉ ይልቃል። ባዶ ኪስን ሙሉ ጭንቅላት ይሞለዋል። ባዶ ጭንቅላትን ግን ሙሉ ኪስ አይሞላውም። ሰዎች ከጥበበኞች ጋር ሲውሉ ጥበበኞች ይሆናሉ። ከመርዘኞች ጋር ሲውሉ ደግሞ መርዘኛ ይሆናሉ። ከጥበበኛ ጋር የዋለ ከመርዛም ቢገጥም እንኳን መርዙን ወደ ማር ለመቀየር አይቸገርም። ይህ ደግሞ የሚቻለው ከማማረር በማሳመር ሂደት ውስጥ ነው።

ሰዎች ጥበበኛ ለመሆን እና ሕይወትን ስኬታማ ለማድረግ ብዙ ዲግሪ መሰብሰብ፣ ብዙ ሰርተፊኬቶችን መሰብሰብ፣ ብዙ ሃብት ንብረት መሰብሰብ፣ ብዙ ሰዎችን በዙሪያቸው መሰብሰብ እና መዳረሻ የሌለው የምኞት ፈረስ መጋለብ ትክክለኛው መንገድ ይመስላቸውና ከአንዱ ጫፍ ወደ አንዱ እየተዋከቡ ዘመናቸውን መዳረሻ የሌለው ጉዞ ያደርጋሉ። መጓዝ ብቻ። ሕይወት የሌለው መንገድ። ሕይወት ግን እንደዛ አይደለችም። የጎረስነውን አጣጥመን ሌላ መጉረስን ትሻለች። ያኘክነውን ውጠን ሌላ ማኘክን ታዛለች። እየሰራን መኖርንና እየኖርን መስራትን ትፈልጋለች። ለዚህም ቆም ብሎ ማስተዋልን፣ ለሆዳችን በቀን ሶስቴ ምግብ እንደምናቀብለው ውሃ እንደምናቀብለው፣ ምሳ ቁርስ እራት ከደላም መክሰስ እንደምናቀርብለት ለአዕምሮአችንም ድግሞ የአዕምሮ ምግብ (የሚመጥነው መጽሃፍ፣ ስልጠና፣ ሽርሽር ወዘተ) ማቅረብ ይገባናል ማለት ነው። ይህ ሕይወታችንን ያሳምርልናል። ማማረርን ይቀንስልናል።


ለዘመናት ካነበቡት መጻሕፍትና ከቀሰሙት ጥበብ ከሚያጋሩ፣ በጥበብ የበለጽጉና በእውቀት ከቀደሙ ሰዎች ጋር በመቅረብ አጫጭር ስልጠናዎችን በመውሰድ፣ የኑሮ ዘዴን ተረድቶ መኖር አማራጭ የሌለው 'ከማማረር የማሳመር' መንገድ ነው። በዚህ መንገድ መሄድ የማይነኩ አደገኛ የሕይወት ፈንጂዎችን ሳንነካ፣ የማይታለፉ መልካም አጋጣሚዎች ደግሞ ሳያመልጡን የሕይወት እሾህን ተጠንቅቀን የሕይወት እሸትን እየበላን በሰላምና በጤና ከዘመን ዘመን እንድንሻገር ያስችለናል። የሕይወትንም መዓዛ እንድናሽት፣ ጣዕሟንም እንድናጣጥም መልካም ዕድል ይሰጠናል።

በዚህ ስኬታማ የመኖር ቀመር ተቀምረን፣ ራሳችንን ከብክነት እና ከከንቱነት ጠብቀን፣ ቀስ በቀስ እንቁላል ከሆነው ሕይወታችን ላይ ቅርፊቱን ሰብረን በመውጣት አዲስ የጠቢባን ዓለምን ለመቀላቀል 'ከማማረር ማሳመር' በምትባለው የጥበብ ዶሮ ታቅፎ መፈልፈል የብልሆች ቀዳማይ ምርጫ መሆን አለበት። ያኔ ታዲያ በፍቅር ሕይዎታችን፣ በትምህርት ሕይወታችን፣ በትዳር ሕይወታችን፣ በስራ ሕይወታችን፣ በቤተሰብ ሕይወታችን፣ በልጅ አስተዳደግ ሕይወታችን፣ በቢዝነስ ሕይወታችን፣ በአመራር እና አስተዳደር ሕይወታችን፣ በተግባቦት ሕይወታችን፣ በሰው ፊት ተናግሮ የማሳመን ክህሎት ሕይወታችን ወዘተ ዕድገትን ተመንድገን መኖር ስንጀምር የሕይወታችን የማማረር ምዕራፍ ተዘግቶ የማሳመር ምዕራፍ ሲከፈት ዝም ብሎ ምድር ላይ የመመላለስና ሕይወትን አጣጥሞ ኖሮ የማለፍ ልዩነቱ ይገለጥልናል። ከዚያም ጸሃይ ስትወጣ 'ከማማረር የማሳመርን' መንፈስ ተላብሰን፣ ከጸሃይ እኩል ደምቀን ቀናችንን በረከታችንን ለመቀበል እንወጣለን። ጸሃይም ስትጠልቅ ቀኑን ሙሉ ያዘመርነውን የቅንነት እና የማሳመር አዝመራችንን ተከናንበን እጅግ ጥልቅ ወደሆነው ሰላማዊ እንቅልፋችን ከጸሃይ እኩል እንጠልቃለን። በዚህ መልክ ከጸሃይ እኩል ሲነጋ እየነጋን ሲመሽም እየመሸን የተፈጥሮን ዑደት በመከተል እንረካለን፣ 'ከማማረር ማሳመርም' ብዙዎችን እያሳመረ ወደ ፊት ይቀጥላል።

እንዳይታለሉ! ከገጽ 1 የዞረ

ይህ ማለት አንድ ግለሰብ ኢንተርኔት ለማግኘት ወደዚህ የኮምፒውተሮች ስብስብ በቴሌኮሚዩኒኬሽን ድርጅቶች በኩል ወደ ስብስቡ (ኔትወርክ) ይቀላቀላል። በሌላ አባባል ወደ ኢንተርኔቱ ለመግባት እንከፍላለን እንጂ ኢንተርኔት እራሱ የሚያስከፍል አይደለም። ታዲያ ኢንተርኔት ከላይ በጠቀስኩት ሃሳብ መሰረት የአንድ ድርጅት ወይንም የአንድ አገር ንብረት አይደለም ማለት ነው።

እኤአ በ2019 ዓም እንደ ጉግል እና የመሳሰሉት ድርጅቶች ባደረጉት ጥናት ከ1.5 ቢሊዮን በላይ ድረ-ገጾች እንዳሉ ጠቅሰዋል። ይህ ቁጥር ከ2014 ዓም ጀምሮ በየዓመቱ ከ30 እስከ 40 ፐርሰንት እደገት እያሳየ እንደመጣም ገልጸዋል። በጣም የሚገርመው ነገር ቢኖር ይህን የሚያክል የመረጃ መረብ (ኢንተርኔት) ተጠቃሚ ሰዎች ምን ዓይነት የማታለያ ነገሮች ሊኖሩ እንደሚችል አለመገመታቸው ነው።



የውሸት ዜና (ፌክ ኒውስ)

በአሁኑ ሰዓት የመላውን ዓለም ህዝብ እየረበሸ እና ኢኮኖሚም እያቃወሰ የሰው ሕይወት ለመጥፋት ምክንያት የሆነ ነገር ቢሆን የውሸት ዜና (ፌክ ኒውስ) ነው። ስለ ሀሰተኛ ዜና ወይንም ፌክ ኒውስ የሚጽፉ ሰዎችን ማንንነት ለማውራት ሳይሆን እንዴት እንለየው ወይንም እንቀንሰው ስለሚለው ብናወራ ይጠቅማል ብዬ አስባለው። ከ99 በ መቶው በላይ የውሸት ዜና የሚሰራጭበት መንገድ ቢኖር ፌስቡክ እና ትዊተር ናቸው። አንድ ነገር እዚህ ጋር ልብ ማለት ያለብን ቢኖር ፌስቡክም ሆነ ትዊተር አላማቸው የዜና ማንበቢያ ድረ-ገጽ አለመሆናቸውን ነው። ይህ ማለት ፌስቡክ ላይ ተጽፎ የምናገኘውን ነገር ትክክል ነው ብለን መቀበል እንደሌለብን ነው። እንደው ምን አልባት የምናምነው ግለሰብ ወይንም ድርጅት ፌስቡክ ወይ ትዊተር ገጽ ቢሆን እንኳን መረጃውን ጉግል በማድረግ ሌላ የዜና ማስተላለፊያ ደረ ገጾች ለምሳሌ ያህል ቢቢሲ፣ ሲኤንኤን የመሳሰሉት ላይ መኖሩን ማረጋገጥ ይገባል። የዜና ወይንም የትክክለኛ ወቅታዊ መረጃ ፍለጋ ፌስቡክ እና መሰሎቹን ብቻ መጠቀም ተገቢ አይደለም።

በቀላሉ ሃብታም ይሁኑ የሚል ርዕስ ያላቸው ኢሜሎች (BECOME RICH OVER NIGHT EMAIL SCAMS)

ስንቶቻችን እንደዚህ አይነት ኢሜሎች ሲደርሱን እውነት መስሎን ተሸውደን ይሆን? በኢሜሉ ላይ የሚያንቡት ነገር በጣም የሚያጓጓ ነው አብዛኛዎቹ ኢሜሎች አጻጻፋቸው ቢለያይም ሃሳቡ ግን አንድ ነው። እንደዚህ አይነት ኢሜል ደርሰዎት የማያውቁ ከሆነ ትንሽ ብናብራራው መልካም ይመስለኛል። የኢሜሉ መልዕክት እንዲህ ይላል "ቤትዎ ቁጭ ብለው በአንድ ሰአት ስራ ብቻ እስከ 400 ዶላር ያግኙ" (MAKE UP TO $400 PER DAY FROM YOUR HOME WITH ONLY 1 HOUR OF WORK)። እስኪ አስቡት ማን ነው አንድ ሰዓት በመስራት ብቻ 400 ዶላር ወይንም 12,800 በቀን ውስጥ ማግኘት የሚጠላ? ታዲያ እንዴት ነው ብለው ነገሩን ማጣራት ሲጀምሩ ማለትም ለበለጠ መረጃ ኤሜሉ ላይ ይጫኑት የሚለውን ማስፈንጠሪያ (ሊንክ) ሲጫኑት ወደ አጨበርባሪው ድረ-ገጽ ይወስዶታል። ድረ-ገጹ ላይ ነገሩን እውነት የሚያስመስሉ የተለያዩ ሰዎች ምስክርነት ከነፎቷቸው ቪዲዮ እና ንግግሮችን ያገኛሉ። በዚህ ሰዓት በውስጦ ይህ ነገር እውነት ይሆን እንዴ የሚል የነበረው ጥርጣሬ ወደ እርግጠኝነት ያዘነብላል። በመቀጠልም "አሁኑኑ ይመዝገቡና ስራውን ይጀምሩ" የሚለውን ማስፈንጠሪያ (ሊንክ) ሲጫኑት 99 ዶላር ወይንም 3170 ብር በመክፈል አባል ይሁኑ ይሎታል። ምናልባት ከኢትዮጵያ ውጪ የሚሰሩ ክሬዲት ካርዶች ባለመኖራቸው ብዙ ሰው ከዚህ ደረጃ ላያልፍ ይችላል። አጭበርባሪዎቹ ግን እዚህ ደረጃ ድረስ መሄዳችንን ድረ-ገጹ ላይ ባለ መከታተያ ኮድ (ትራኪንግ ኮድ) መሰረት ደጋግመው ከኢትዮጵያ ወጪ ያሉ ዘመዶችዎ እና ወዳጆችዎት ብሩን እንዲከፍሉልዎት የሚያስረዳ ኢሜሎችን መላክ ይጀምራሉ። ይህን ስላችሁ በጣም ብዙ የሆኑ ዘመድ እና ጓደኞቼ አሜሪካ እና ካናዳ እያለሁ ይልኩልኝ ነበር።

እስኪ ወደ ዋናው ቁም ነገር እንመለስና ነገሩን እናስበው ለመሆኑ ምን ዓይነት ህጋዊ የሆነ ስራ ነው ቤቴ ቁጭ ብዬ አንድ ሰዓት ብቻ በመስራት ይባስ ብሎ የማላውቀው ሰው በኢሜል አግኝቶኝ ስራ የሚሰጠኝ። ሁለተኛ እንደዚህ አይነት ሰራ የሚያውቅ

ሰው ካለ እንኳን ለምን እራሱ ብቻዉን በቀን ውስጥ 10 ሰአት በመስራት 4,000 ዶላር ወይንም 128,000 ብር የማያገኘው እንዴት ይህን ሚስጥር ለሌላ አሳልፎ ይሰጣል። ሶስተኛ እንደው ስራው እውነት ነው ብለን እናስብ እና እንዴት ይህን የመሰለ ስራ እኔ 99 ዶላር ብቻ በመክፈል ላገኘው እችላለሁ። አራተኛ ከፍዬ ከገባሁ በኋላ ስራው እውነት ሆኖ ብሰራው ይህ የላከልኝ ሰው እንዴት አምነዋለሁ እንደሚከፍለኝ። ነገሩ ዘርዝረን ስናየው በጣም የሚያስቅ የሞኝ ሃሳብ ይመስላል ግን በአለማችን ላይ በቀን ከ20 ሚሊዮን በላይ እንደዚህ አይነት ኢሜሎች ይላካሉ። ይበልጥ የሚያሳዝነው ነገር ግን ከ20 ሚሊዮኑ ወደ 0.1 ፐርሰንቱ ኢሜል ሰዎቹን አታለዋቸው ገንዘብ ይከፍላሉ። ሂሳቡን ብናሰላው 20 ሺ ያህል ሰው በየቀኑ ተሸውዶ ቢያንስ ከ29 እስከ 99 ዶላር ይከፈላል ማለትም በየቀኑ እስከ 2 ሚሊዮን ዶላር በዚህ ኢሜል ምክንያት ብዙዎች ይሰረቃሉ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የናይጄሪያ ፕሪንስ በመባል የሚታወቀው የማጭበርበሪያ ኢሜል በጣም በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ብዙ ገንዘብ የተሰረቁበት መንገድ ነው። ይህም ኢሜል ቢሆን ‘‘ናይጄሪያ ውስጥ ነው የምኖረው እና 2 ሚሊዮን ዶላር ወይንም ዮሮ ከናይጄሪያ ማውጣት ስለምፈልግ ወደ አርስዎ ባንክ ልላከውና እርስዎ 20 ፐርሰንት ወስደው የቀረውን እኔ እውሮፓ ስገባ ከእንድ ወር በኋላ ይልኩልኛል።’’ በዚህ ጊዜ እውነት ይህ ገንዘብ ቢላክሎት የሚኖሩበት አገር መንግስት ይህ ብር ከየት መጣ ብሎ እንደሚጠየቅዎት አስበውት ያውቃሉ? እሱን እንለፈውና ኢሜሉን እንበበው እሺ የሚል ምላሽ ሲሰጡት ቀጣይ ኢሜል እንዲህ የሚል ነው የሚሆነው ‘‘ስለ ትብብርዎት በጣም አመሰግናለሁ ነገር ግን ናይጄሪያ ያለው ባንክ ወደ እርስዎ ባንክ አካውንት ከመላኩ በፊት አካውንቱ የተሳሳተ እንዳይሆን ለማረጋገጥ 400 ዶላር ወደ እኔ አካውንት ትራንስፈር በማድረግ ትራንዛክሽን መታየት አለበት’’ ይላል። ብሩን ከላኩ ቀለጡ ማለት ነው። በሰሜን አሜሪካና አውሮፓ ብዙዎች በዚህ ተታለው ከ100 ሚሊዮን ዶላር በላይ ናይጄሪያ ውስጥ ባሉ አታላዮች ተወስዶባቸዋል።

በዚህ ርዕስ ዙሪያ ያሉ ማጭበርበሪያ መንገዶች ብዙ ከመሆናቸው የተነሳ እንኳን በመጽሔት በመጽሐፍ እንኳን ተጽፎ አያልቅም። እኛ መገንዘብ ያለብን ነገር ቢኖር አንድ ኢሜል የተደረገ ወይንም ፌስብክ ላይ የተጻፈ ነገር እውነት መሆኑ ካጠራጠረን አብዛኛውን ጊዜ እውነት አይደለም (If it sounds too good to be true chances are it’s not TRUE) ። ከዚህም ባለፈ ደግሞ ይህን መረጃ ማረጋገጥ ከፈለግን ጉግል በማደረግ በነገሩ ዙሪያ ላይ ምን ዓይነት መረጋገጫ እንዳለ ማንበብ እንችላለን። በኢሜል ከሚመጡ ነገሮች አስቀድሞ ኢሜሉ እንዳይመጣ ከፈለጉ ኢንተርኔት በሚጠቀሙበት ጊዜ ኢሜል ካላስገቡ ብለው የሚጠይቁ ደረ-ገጾችን ዋና ኢሜል አድራሻዎትን ትተው ሁለተኛ ኢሜል በመክፈት ለእንደዚህ አይነት ደረ-ገጾች ብቻ መጠቀም ይችላሉ። ምክንያቱም ደረ-ገጾቹ ኢሚል አድራሻዎትን ለተለያዩ ማስታወቂያ እና ማጭበርበሪያ ነገሮችን ለሚልኩ ሰዎች ስለ ሚሸጡት ነው። በሚቀጥለው ወር እስከምንገናኝ መልካም ቆይታ ይሁንልዎት።



ከላይ ከተጠቀሱት ጥያቄዎች ለአንዱ
እንኳን አዎ ከሆነ መልስዎት
በ+251 911 62-79-15
ወይንም
+251 118-69-17-99
ደውለው ያነጋግሩን!

PSOF PUBLIC SPEAKING & OVERCOMING FEAR TRAINING

MOTION
የስልጠናው አዘጋጅ
ሞሽን ኮንሰልቴንሲ ኤንድ ትሬኒንግ
አሰልጣኝ
አቶ ብርሃኑ ራቦ

Why Motion?

By Abebe Legesse


Anything in the universe have cause and reason of formation and/or transformation and/or transcendence. But some reasons are the foundation to the other reasons. Such reasons are those that are usual called 'Values. Values are like driving lanes, it guides and leads to aspired destinations, it helps to score records, it helps to make visible spot in the universe. Values are close to self, it exists and persist with and within self, it is not conditional, it is a precondition based on which to act or not is decided.

Maintaining Values requires passion and courage to scarify possessions. The followings are the reasons which maintains Motion and which Motion sacrifices for;

- Trust and Respect: Motion recognizes and upholds the dignity of each person in a spirit of love and it does unto others as it would have them do unto it and it adds value by valuing others. It is committed to meet its interest through meeting needs and interest of others. Motion Trust not only human but even none human creatures in the universe, thus Motions' endeavours are transparent, inclusive and genuine. Motion Respect not only peoples but also ideas and toughs of peoples, thus it believes in the power of synergy and collaboration than exploitation and competition.
- Win-Win Endeavor: Motion's essence shall remain even-handed both in business & nature and social services. It has unwavering commitment to excel in service by synergizing needs of human and nature and own and others interest. Motion opts to give than to receive, Motion believes that there's is sufficient resources in the universe and thus there is no need to move in the direction of exploitation, rather opt for fairness. Motion also believes that any thing that goes comes. So, it strives to let good things to go.
- Originality: Motion holds itself to highest personal and professional standards and also strives to do things out of its capacity and capability. Motion strives to optimize joy and satisfaction to self and others thought cocktailing new and admirable flavours in to all its endeavours. One way to do this is to be critical and creative. Thus, it encourages flexibility, freedom of thought and exposures to adversity.
- Timeliness: Motion works dedicatedly to meet deadlines and exert its maximum effort to be up-to-date. The universe is dynamic, nothing is stationary or static. Thus, keeping rhythm with the dynamism is not only entertaining but also is a roadmap for achievement and excellence. Motion believes and strives to be organized, planed and remain proactive in its endeavours.
- Action and impact: Motion believes that actionable thoughts and impactful actions constitute its essence. So, it won't promote thoughts and ideas that it will not dare to act on and it will not dear to act if the action won't have impact. Motion believes and strives not to be illusive but tangible.

Motion Values are close to humanity and thus to everyone but hard to maintain particularly during the contemporary time, as it exposes to danger and damage emanating from the contrary and controversial nature of human. However, Motion courageously faces the dangers and strives to safe guard the values as it safeguards its vison and mission, without which existence will have no meaning and living and effort without meaning is immoral, temporary and void, but human is not and should not.

Managing and or overcoming the contrary and controversial nature of human, needs strategies and tactics. The strategies and tactic Motion rely on to overcome challenges and progress in service will be presented with the next edition of Green Fire.



ሰውን እንዳይችል የሚያደርገው ምንድን ነው?

በተመስገን አብይ
Motivational speaker

በመጀመሪያ ሰው የሚችል ፍጡር ነው። በዚህ ልንስማማ ያስፈልገናል። ያሰብነውን ከግብ ማድረስ እንችላለን የመቻል አቅማችንን ተጠቅመን። የሀይማኖት ሃገር ውስጥ ሆነን ሰው ይችላል ወይስ አይችልም የሚል ክርክር ውስጥ መግባት አያስፈልገንም። ምክንያቱም ሃይማኖቶቻችን የሚሰጡን መልስ ስላለ።

ሰውን እንዳይችል ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል አንደኛው አለመቻልን ደጋግሞ ማሰብና በአለመቻል ስሜት ውስጥ መኖር ነው። በጣም የሚገርመው ነገር የሚታየውን ግዙፍ ሰውነታችንን እንዲት የማትታይ ነጠላ ሃሳብ አስራ ማስቀመጥ መቻሏ ነው። ለምን ካላችሁኝ እኛ ፍቃድ ስለሰጠናት ነው። አልችልም የሚለውን ሃሳብ በእኛ ላይ እንዲነግስና እንዲቆጣጠረን ፍቃድ ሰጥተነዋልና ነው።

አንድ ሰው ውስጥ እምቅ አቅም አለ። ይህ አቅምና ክህሎት የሚፈስበት አቅጣጫ ይፈልጋል። ይህም የሚሆነው ትኩረት ወዳደረግንበት ነው። አንድ ሰው ሀይሉን አሰባስቦ አንድ ነገር ላይ ሲያውል ውጤታማ ይሆናል። ትኩረት አድርገን መስራት ከቻልን።

ብዙዎቻችን ግን አካላችን ያለው ሌላ ቦታ፣ ሃሳባችንም ሌላ ቦታ ስለሆነ ተኩረት ለማድረግ እጅግ ተቸግረናል። በአንድ ጊዜ አንድ ቦታ መሰብሰብ አልቻልንም። የምናያቸው፣ የምናደምጣቸው እና የምንነካቸው ነገሮች መብዛት አንድ አቅጣጫ አሳጥተውናል። በአንድ ጊዜ ብዙ ቦታ ለመገኘት እንድንሻም ምክንያት ሆነውናል። ስለዚህ እነዚህን ነገሮች መቀነስና መወሰን ያስፈልገናል ማለት ነው።

ያለፈው ድሁፌ ላይ ከማንችላቸው ነገሮች ይልቅ የምንችላቸው ነገሮች ይበዛሉ ብዬ ነበር። በርግጥ ይህን ሃሳብ ሁሉም ሰው ለመረዳት አይችልም ትኩረታችን መቻል ላይ ካልሆነ በስተቀር። የምንፈልገው ውጤታማ መሆን ከሆነ ትኩረታችን ውጤት ላይ ነው መሆን ያለበት። እርግጥ ነው ብዙ መሰናክሎች አሉ ቢሆንም ፍላጎታችን ውጤት ስለሆነ ትኩረታችንን እዚሁ ላይ መጠበቅ አለብን።

ትልቁ የሰው ልጅ አቅም በትናንሽ ግን ትልቅ በሚመስሉ የሃሳቦች አጥር ታጥሯል። አቅሙ ያለው እኛ ውስጥ ነው አጥሩንም የሰራነው እኛው ነን ስለዚህ የሰራነውን አጥር ሌላ ሰው መጥቶ እንዲያፈርስልን አልያም እንዲያነሳልን መጠበቅ መፍትሄ አይደለም።

ትኩረት ወዳደረግንበት ሁሉ ሃይል ይፈሳል። ያለን አምቅ አቅም በየቦታው ፈሶ ትርጉም አልባ ህይወት እንዳንኖር ትኩረት የምናደርግበት ነገር ለይተን እንወቅ።



INTERSTING FACTS



Have you ever considered how big numbers are especially when we are talking about a billion. So, let's do a small exercise. If I say I was here **1000** seconds ago that means it is ***16 minutes and 40 seconds ago***. So, let's say **1,000,000** seconds ago whic is ***11 days and a half ago***. Let's take it to the next level what if I say I was here **1,000,000,000** (One Billion) Seconds ago? I am sure you are thinking somewhere around 45 to 60 days ago right. No not even close, one billion seconds ago means its ***31 years, 251 days, 13 hours, 35 minutes ago***. So now we have seen how big of a number is when we talk about billions, so here are more fun facts about the world of Internet



160 billion emails are sent daily, and out of the 160 billion about 97% (155.2 billion) of them are Spam also known as junk mail.



As of 2019 Facebook has 2.234 Billion users. Approximately 30% of the world's population has Facebook account.



As of 2019, there are more than 2 billion computers and 4.5 billion mobile phones in the world. Out of the 4.5 billion mobile phones, about 3 billion are smart phones, from those 2.5 billion of them are connected to the Internet.



The Internet took just four years to reach its first 50 Million Users. Television took 13 years. While the radio took 38 years to reach the same number of users

Google gets 1 billion searches a day, while YouTube a company owned by Google gets about 3.25 billion video views per month.

As of March 1, 2020 The internet is 11312 days old which is about 31 years old



95 million photos are uploaded on Instagram every day. The sad thing is that 70% of Instagram posts don't get seen.

The first website created was HTTP://INFO.CERN.CH/ and it is still online. It's a basic HTML site, and the page contains a few lines of text

A place to be every FRIDAY @ 6PM

WISDOM NIGHT is a program that has been held Every Friday Night for the past 6 years at Motion consultancy and training PLC. For the past five years with the intention of sharing wisdom among people who are dedicated to taking their lives to a whole new level.
Since the beginning of our program we had the privilege of hosting so many incredible people.



Wisdom Night Program format

- The session starts at 6:00 PM sharp,
- The presentation part of the session takes 45 minutes,
- After the presentation there is a Q & A session

If you would like to share your life experiance call Yonatan at +251 911 75-30-88

አስታውሱ
ዊዝደም ናይት መግቢያም ሆነ መውጫ በነጻ መሆኑን አይርሱ። ዓርብ ከምሽቱ 12 ሰዓት እንጠብቆታለን
አድራሻ ፡ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ሸገር ህንጻ 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 202





it's possible to

work hard without stressing!

- CONSULTANCY
- COUNSELLING
- RESEARCH
- DEVELOPMENT
- TRAINING
- COACHING

LET US SHOW YOU HOW!

Call or Email us NOW

+251 118 69-17-99

+251 911 62-79-15

mctethio@gmail.com

WWW.MOTIONETHIOPIA.COM

MOTION CONSULTANCY & TRAINING PLC

NEAR URAEL CHURCH ON SHEGER BUILDING OFFICE #201 ADDIS ABABA, ETHIOPIA